# ደንብ

MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS
የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ

**ተዛማጅ ምንጮች፡-** CGA-RA, IED, IHC-RA, IKC-RA, IOE-RA, IOF-RA, ISD, JEA-RD, JEB-RA, JEC-RA, JEG-RA

**ኃላፊነት የሚመለከተው ጽ/ቤት፡-** Office of the Deputy Superintendent of Schools; Office of the Chief Academic Officer

## የ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መመረቂያ መስፈርቶች

I. **ዓላማ**

የሜሪላንድ ስቴት እና የሞንጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) አስፈላጊ የመመረቂያ መስፈርቶችን የአፈፃፀም ሂደት ማሳወቅ

II. **ትርጓሜ**

A. በዚህ ደምብ መሠረት፣ብቃት ያለው/ያላት ተማሪማለት 18 ዓመት ወይም ከዚያ በላይ እድሜ ያለው/ያላት ማለት ነዉ።

B. የሜሪላንድ አጠቃላይ የፈተና ምዘናዎች (MCAs) በሜሪላንድ ስቴት የትምህርት ዲፓርትመንት (MSDE) በተገለጸው መሰረት በተወሰኑ ኮርሶች ይዘት ላይ የተዘጋጁት የትምህርት ፈተናዎች የተማሪዎችን የትምህርት ችሎታ እና እውቀት ይለካሉ። ተማሪዎች የሚመለከታቸውን ኮርሶች ከጨረሱ በኋላ እነዚህን መመዘኛዎች/ፈተናዎች ይወስዳሉ።

C. MCPS የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የኮርስ መግለጫ መጽሔት በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የሚሰጡትን ሁሉንም የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ኮርሶች የሚዘረዝር አመታዊ መጽሔት ነው፣ እንዲሁም ስለ መመረቂያ መስፈርቶች፣ የፈተና ምዘናዎች፣ የሥራ ልምምዶች፣ ጣምራ/ድርብ የምዝገባ እድሎች እና ልዩ ፕሮግራሞችን ይዘረዝራል። የMCPS ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ኮርስ መግለጫ መጽሔት (Bulletin) በየጊዜው እየተሻሻለ በተከታታይ ታትሞ ይወጣል። የ MCPS ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ኮርስ መግለጫ እና ተሻሽለው የተጨመሩ ነገሮች በ MCPS ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ኮርስ መግለጫ ድረ-ገጽ ላይ ታትመው ይወጣሉ።

D. ኦሪጅናል ክሬዲት ማለት ተማሪው(ዋ) ከዚህ በፊት ክሬዲት ያላገኘ(ች) ከሆነ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ኮርስ ወይም የተፈቀደ አቻ የኮሌጅ ኮርስ በተሳካ ሁኔታ ሲጠናቀቅ የሚገኝ ክሬዲት ነው።

E. የተማሪ አገልግሎት ትምህርት (SSL) በትምህርት ቤት ወይም በማህበረሰብ ውስጥ ነዋሪ የሆነ(ች) ተማሪ ማሟላት ያለበ(ባ)ት የማይከፈልበት ክንውን ሲሆን ይህም ለአንድ ግለሰብ፣ ወይም ቡድን፣ የትምህርት ቤትን ወይም የማህበረሰብን ፍላጎት ለማሟላት የሚሰጥ አገልግሎት ነው። የሥራው አይነት እና ሥራውን ስፖንሰር የሚያደርግ(ጉ) ግለሰብ/ቡድን በ MCPS ተቀባይነት ያገኙ መሆን አለባቸው።

F. ክሬዲት ማስተላለፍማለት፡- ተማሪው(ዋ) በሚመዘገብበት/በምትመዘገብበት የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ትምህርት ቤት ርእሰ መምህር/ተወካይ የሚወሰን ከ MCPS ውጭ በሌላ ትምህርት ቤት የኮርስ ስራ የተገኘ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲት ነው። የሜሪላንድ ደንብ ኮድ (COMAR) §13A.03.02.12 MCAs ተማሪዎችን ከተመሳሳይ ኮርሶች የዝውውር መመዘኛ ነፃ ማድረግን

ጨምሮ ተጨማሪ የክሬዲት ዝውውር መስፈርቶችን ይገልጻል።

III. **ቅደም-ተከተሎች**

A. ምዝገባና ምደባ

1. አማራጭ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ፕሮግራም ካልተፈቀደለ(ላ)ት በስተቀር አንድ ተማሪ ከ 8ኛ ክፍል በላይ የአራት ዓመት መደበኛ የትምህርት ፕሮግራም በአጥጋቢ ሁኔታ ማጠናቀቅ አለበ(ባ)ት። (ክፍል III.F. ላይ ስለ አራት ዓመት የትምህርት የምዝገባና ምደባ አማራጮችን ያገናዝቡ)

2. 8ኛ ክፍል የጨረሰ(ች) ተማሪ የስቴት እና የአካባቢ ት/ቤት ክሬዲት፣ምዘናዎችን፣እና SSL ተፈላጊ መስፈርቶችን ካሟላ(ች) ከአራት ዓመት በላይ በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪነት አይቀጥልም/አትቀጥልም።

3. እያንዳንዱ ተማሪ በሜሪላንድ ፐብሊክ ስኩልስ እስከ አራት አመት ድረስ በየአመቱ የሂሳብ ትምህርት ኮርስ መውሰድ አለበ(ባ)ት። የዚህ ኮርስ ተፈላጊነት በመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት እያሉ ለሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የሂሳብ ኮርሶች ለተመዘገቡት አይሠረዝላቸውም። እነዚህን አስፈላጊ መስፈርቶች የሚያሟሉ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ኮርሶች በየዓመቱ MCPS የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ኮርስ መጽሔት ላይ ይወጣል/ይታተማል። ክፍል III.C.3. ላይ እንደተገለጸው ተማሪዎች ጣምራ ኮርስ በመውሰድም ይህንን ተፈላጊ መስፈርት ሊያሟሉ ይችላሉ።

B. በሞንትጎመሪ ካውንቲ የሜሪላንድ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ዲፕሎማ

ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ተፈላጊ መስፈርቶች ያሟሉ ተማሪዎች የሜሪላንድ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ዲፕሎማ ያገኛሉ። MCPS የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ኮርስ መጽሔት (Bulletin) እና ሌሎች ተዛማጅ ከስቴት እና ከአካባቢ ት/ቤት ለመመረቂያ ተፈላጊ መስፈርቶች እንደተማሪው(ዋ) ሁኔታ በዘጠነኛ ክፍል የመጀመሪያ ዓመት ሊለያይ ይችላል።

1. ክሬዲት፣ የተማሪ አገልግሎት ትምህርት (SSL)፣ እና የሜሪላንድ አጠቃላይ የትምህርት ችሎታ ምዘና (MCA) መስፈርቶች

   a) ክሬዲት

      (1) በሜሪላንድ ደንብ እና በሞንጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ ፖሊሲ IED ላይ እንደተገለጸው፣የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ትምህርት አውድ እና መዋቅር ቢያንስ በስቴቱ ከሚፈለጉት ግዴታዎች በላይ ቦርዱ ለመመረቂያ አስፈላጊ የሆኑ ልዩ ሁኔታዎችን ሊደነግግ ይችላል።

         (a) MCPS ለመመረቂያ 22 ክሬዲቶች የሚያስፈልጉ ሲሆን ከዚህ ውስጥ በእንግሊዝኛ፣ ማህበራዊ ጥናት፣ ሳይንስ፣ ሂሳብ፣ የሰውነት ማጎልመሻ፣ የጤና ትምህርት፣ስነጥበብ፣ እና በቴክኖሎጂ ትምህርት 19.5 ክሬዲቶችን በስኬታማነት በማጠናቀቅ ይሆናል።

         (b) እያንዳንዱን መመዘኛ የሚያሟሉ ክሬዲቶች እና ኮርሶች MCPS የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የኮርስ መጽሔት (Bulletin) ላይ በየዓመቱ ይወጣል።

(c) በምርጫ የሚወሰዱ/ኤሌክቲቭ ክሬዲቶችን ከቀረቡት የኮርሶች ዝርዝር ማናቸውንም ተጨማሪ መምረጥ ይቻላል።

(2) ተማሪ ለመግባት የሚፈልግበት/የምትፈልግበት እያንዳንዱ የኮሙኒቲ ኮሌጅ፣ ኮሌጅ፣ ወይም ዩንቨርስቲ MCPS ከሚጠይቀው የመመሪቂያ መስፈርት የተለየ የራሱ የመግቢያ መስፈርት ሊኖረው ይችላል። ስለ ድህረ-ሁለተኛ ደረጃ ፕሮግራሞች ወይም ለመግባት የሚታሰቡ ት/ቤቶች ማናቸውም ተጨማሪ የመግቢያ መስፈርቶችን ተማሪዎች እና ወላጆቻቸው/ሞግዚቶቻቸው በጥንቃቄ መመርመር አለባቸው።

(3) ክሬዲት ያላቸው/ክሬዲት የሌላቸው ኮርሶች እና ተተኪ ውጤቶች

(a) MSDE ወይም MCPS ለመመረቅ በሚያስፈልጉ ኮርሶች ላይ ከዚህ በታች በክፍል II.B.2 ከተገለጹት የተወሰኑ ሁኔታዎችን በስተቀር በክሬዲት/ያለክሬዲት መጠቀም አይቻልም። የችሎታ ማረጋገጫ ሠርተፊኬት ኮርስ (Section III.C ላይ የተገለፀውን የዲፕሎማ ማረጋገጫ ይመልከቱ) ክሬዲት/ያለክሬዲት ተግባራዊ አይሆንም።

(b) አንድ ተማሪ ኮርስ በድጋሚ ሲወስድ/ስትወስድ፣MCPS ደንብ IKA-RA የውጤት አሰጣጥ እና ሪፖርት አቀራረብ ድንጋጌ መሠረት በድጋሚ በተወሰደ ኮርስ የተገኘው ውጤት አማካይ ድምር ውጤት ላይ ይካተታል።

b) የተማሪ አገልግሎት ትምህርት (SSL)

ተማሪዎች 75 ሰዓት የተማሪ አገልግሎት ትምህርት (SSL) ማጠናቀቅ አለባቸው። SSL ከበጎ ፈቃደኝነት ወይም ከማህበረሰብ አገልግሎት የሚለየው ተማሪዎች በትምህርት ቤት የተማሩትን በህይወት ተሞክሮ/በነባራዊ የሥራ ዓለም ተግባራዊ በማድረግ የትምህርት ችሎታቸውን እንዲያሻሽሉ እድል ይሰጣል። በዚህም እነርሱ በትምህርታቸው እና በሥራ አገልግሎታቸው ያገኙትን ልምድ በተግባር ላይ ያንፀባርቃሉ። SSL ተፈላጊ መስፈርቶች፣ ተቀባይነት ያለው የአገልግሎት ሥራ፣ እና መዝግቦ የመያዝ አሠራር MCPS SSL ድረ-ገጽ ላይ ይገኛል።

c) የሜሪላንድ አጠቃላይ ምዘና/ፈተና (MCA)

ተማሪዎች MSDE የተደነገገውን የምዘና መስፈርቶች ማሟላት አለባቸው። MCA መስፈርቶች ተማሪው(ዋ) ኮርስ ለመውሰድ በተመዘገበ(ች)በት አመት ወይም ተማሪው(ዋ) ለመጀመሪያ ጊዜ ዘጠነኛ ክፍል በተመዘገበ(ች)በት አመት ሊለያይ ይችላል። እነዚህ መመዘኛዎች በስቴት እና በአካባቢ ለመመረቂያ መሟላት ያለባቸውን መስፈርቶች በያዘዉ MCPS የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የኮርስ መጽሔት እና ተጨማሪ ተዛማጅ የኮርስ ዝርዝር ውስጥ ይገኛል።

2. የመመረቂያ መስፈርቶችን ለማሟላት ክሬዲት ስለ ማዛወር/ማስተላለፍ

a) ከሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ውጪ የተገኘ ክሬዲት ማስተላለፍ/ማዛወር

(1) አንድ ተማሪ የሜሪላንድ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ዲፕሎማ ለማግኘት የሚችለው/የምትችለው፣ ተማሪው(ዋ) ከሌሎች የመመረቂያ መመዘኛዎች በተጨማሪ በሜሪላንድ ፐብሊክ ስኩልስ ከመመረቂያ ወቅት አስቀድሞ ባለው አንድ ሙሉ ሴሚስተር መከታተል ከቻለ(ች) ብቻ ነው።

(2) ከካውንቲ ውጭ የሆኑ እውቅና ባላቸው ፐብሊክ ስኩልስ ካልሆኑ ት/ቤቶች የተገኙ ክሬዲቶች በርዕሰ መምህሩ ተቀባይነት ማግኘት አለባቸው፥ እና ተነፃፃሪና ተገቢ ወደሆነ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ኮርስ ክሬዲት መቀየር አለባቸው።

(a) ትራንስክሪፕት ላይ ኮርስ ያጠናቀቁበት ውጤት በፊደል የተሰጠ (A-E) ከሆነ ወይም ሌላ ማስረጃ ሲቀርብ፣ ትምህርት ቤቶች በተማሪው(ዋ) ትራንስክሪፕት ላይ ውጤቶቹን በፊደል ማስቀመጥ አለባቸው።

(b) ውጤት በፊደል ካልተጻፈ ት/ቤቶች ተማሪዎች ክሬዲት ላገኙባቸው ኮርሶች "XY" እና ክሬዲት ላላገኙባቸው ኮርሶች "XN" መመዝገብ አለባቸው።

(3) ከዩናይትድ ስቴትስ ውጭ የተገኘን የኮርስ ሥራ ክሬዲት ማስተላለፍ/ማዛወር የሚቻለው ርእሰ መምህሩ MCPS ዓለም አቀፍ የምዝገባ እና ምደባ ክፍል ከደህንነት፣ ትምህርት፣ እና ስኬታማነት ዩኒት ጋር በመመካከር ሲወስን ነው።

(4) SSL ተፈላጊ መስፈርት በተመዛዛኝ የሚታሰበው ለመጀመሪያ ጊዜ ከ 6ኛ ክፍል በላይ ወደ MCPS ለሚገቡ ተማሪዎች ነው።

(5) የሕዝብ ትምህርት ቤት ያልሆነ ወይም ከስቴት ውጪ ከሆነ ትምህርት ቤት የተዛወሩ ተማሪዎች COMAR ላይ በተገለጹት ሁኔታዎች መሠረት ከአንድ ወይም ከዚያ በላይ MCAs ነፃ ሊሆኑ ይችላሉ።

(a) በሲንየር አመታቸው የመጀመሪያ ሴሚስተር ከጨረሱ በኋላ የህዝብ ትምህርት ቤት ያልሆነ ወይም ከስቴት ውጪ ከሆነ ትምህርት ቤት ወደ MCPS የተዛወሩ ተማሪዎች ከ MCA መስፈርቶች ነፃ ናቸው።

(b) ነገር ግን፣ እነዚህ ተማሪዎች የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት በጀመሩበት ወቅት በሜሪላንድ የህዝብ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተከታትለው ከሆነ፣ በሜሪላንድ የህዝብ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ለተማሩበት ጊዜ MCA መስፈርቶች ተገዢ ሊሆኑ ይችላሉ።

(c) ከተቀባዩ ት/ቤት ርእሰመምህር ሲጠየቅ፣የጋራ ተጠያቂነት ዲፓርትመንት COMAR ላይ በተገለጹት መመዘኛዎች መሠረት ተማሪው(ዋ) ከአንድ ወይም ከዚያ በላይ MCAs ነፃ መሆን ይችል/ትችል እንደሆን ለመወሰን በርእሰ መምህሩ የፀደቁትን በዝውውር የተገኙ ክሬዲቶችን ይገመግማል።

(6) በሲንየር ዓመት ላይ ሆነው ወደ MCPS የገቡ ተማሪዎች በቦርድ ፖሊሲ IED የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ትምህርት ማእቀፍ እና መዋቅር ላይ እንደተደነገገው፣ ቢያንስ በስቴት ደረጃ ለመመረቂያ ማሟላት ከሚገባቸው በላይ ሌሎች

የመመረቂያ መስፈርቶች ይታለፍላቸዋል። እንደነዚህ ዓይነቶቹ ተማሪዎች MSDE ከተደነገገው የመመረቂያ መስፈርቶች ያለፈ MCPS ተፈላጊ ተጨማሪ የሂሳብ ክሬዲት እና በሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት ግማሽ ክሬዲት ይታለፍላቸዋል።

(7) ተማሪዎች በሲንየር ዓመታቸው የመጨረሻ ሴሚስተር ላይ ከአንድ የሜሪላንድ የህዝብ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ወደ ሌላ የሜሪላንድ የህዝብ ት/ቤት የተዛወሩ እንደሆነ እና ለምረቃ መሟላት ያለባቸው ሁሉ ተሟልቶ ከሆነ፣ በርእሰ መምህሩ(ሯ) ስምምነት፣ ወይም ከአንድ በላይ የአካባቢ ትምህርት ሥርአት ያለበት ከሆነ የአካባቢ ትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንቶች ከተስማሙ ከሁለቱ በአንደኛው የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት መመረቅ ይችላል/ትችላለች።

3. በመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት የሚሰጡ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ኮርሶች

a) የሥርዓተ ትምህርት እና የትምህርት ፕሮግራሞች ጽ/ቤት (OCIP) ተባባሪ ሱፐርኢንተንዳንት የትምህርት ኦፊሰር ለሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ክሬዲት የሚያስገኙ በመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት መሰጠት ያለባቸውን የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ኮርሶችን፣ ባሉት ፕሮግራሞች እና መገልገያዎች ላይ ምን ዓይነት ተፅእኖ ሊያስከትሉ እንደሚችሉ ከገመገሙ በኋላ፣ እና ከፍተኛ ችሎታ ያላቸው መምህራን ማግኘት መቻሉ ታሳቢ ተደርጎ ለመወሰን ይችላሉ። OCIP ስርዓቱን ከመተግበሩ በፊት በጥቂቱ ትምህርት ቤቶች ኮርስ በመስጠት የሙከራ ጥናት ሊያካሂድ ይችላል።

b) የሚከተሉት መስፈርቶች በጠቅላላ ከተሟሉ በመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት እያሉ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት መመረቂያ ክሬዲት ማግኘት ይቻላል፦

(1) ተማሪው(ዋ) የአካባቢ ት/ቤትን ሥርዓተ ትምህርት ዓላማ በማሟላት/በመፈጸም የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ኮርስ ከወሰደ(ች)።

(2) መምህሩ(ሯ) የኮርሱን እና የሚያስተምረውን/የምታስተምረውን የትምህርት ኮድ ሠርተፊኬት አስፈላጊ ነገሮችን ያሟላል/ታሟላለች።

(3) የሁለተኛ ደረጃ ሥርዓተ ትምህርት ተምሮ(ራ) ከሆነ።

(4) የመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎችም ልክ እንደ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች ተመሣሣይ መስፈርቶችን ማሟላት እና የመጨረሻ ውጤት A፣ B፣ C፣ ወይም D ማግኘት አለባቸው።

5) በተለይ ለምረቃ አስፈላጊ የሆነ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ኮርስ በመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት ለሚገኙ ተማሪዎች ክሬዲት ለማግኘት ከተሰጠ፣ተማሪዎች የተደራጀ የኮርሶች ቅደም ተከተል መከተል አለባቸው።

C. ክሬዲት ለማግኘት ያሉት አማራጮች

1፡ MCPS ከትምህርት ቀናት ውጪ የሚሰጣቸው ኮርሶች

a) ተማሪዎች ከመደበኛው የትምህርት ቀናት ወይም ከመደበኛ የትምህርት ዓመት ውጪ MCPS የሚሰጣቸውን የትምህርት ዕድሎች በመጠቀም የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ክሬዲት ለማግኘት ይችላሉ።

b) ስለ ኮርሱ ኃላፊነት ያለው MCPS ኃላፊ ተማሪው(ዋ) ያገኘ(ች)ውን የፈተና ውጤት እና ጠቅላላ ክሬዲቶችን ለተማሪው(ዋ) የአካባቢ ት/ቤት ረጅስትራር ያሳውቃል/ታሳውቃለች። ከመደበኛ የትምህርት ቀናት ውጪ MCPS በሚሰጣቸው ኮርሶች የተገኙ ውጤቶች ድምር የክፍል ነጥብ አማካይ ስሌት ዉስጥ ይካተታሉ።

c) ተፈላጊ የሆኑ ክሬዲቶችን በማሟላት ከሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት በሰመር ፐሮግራም ለመመረቅ የሚፈልጉ ተማሪዎች በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ደንብ CGA-RA ላይ የተገለጹትን ቅድመሁኔታዎች እንዲያሟሉ ይጠበቃልየሰመር ት/ቤት ፐሮግራም

2. ከሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ውጪ በሌሎች ተቋማት የተሰጠ ኮርስ ክሬዲት

a) ከሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ውጪ ባሉ ተቋማት ክሬዲት ኖሯቸው ከሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የመመረቂያ ኮርሶችን ለማሟላት የሚያመለክቱ ተማሪዎች ለኮርስ ከመመዝገባቸው አስቀድሞ እንደሚከተለዉ ከርእሰ መምህር ይሁንታ ማግኘት ይኖርባቸዋል፦

(1) የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች ከሁለተኛ ደረጃ ት/ቤታቸው ርእሰ መምህር ይሁንታ ያገኛሉ።

(2) እድሜአቸው አነስተኛ የሆነ በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የሚገኙ ተማሪዎች ይሁንታ ማግኘት ያለባቸው ትምህርት ከሚከታተሉበት የአካባቢያቸው ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ርእሰ መምህር ነው።

b) ለኮርስ ሥራ የርእሰ መምህር ይሁንታ፣ ከዚህ በታች ክፍል III.C.3 ላይ እንደተገለጸው ለጣምራ ትምህርት ምዝገባ/dual enrollment በሚከተሉት ላይ የተሞረኮዘ ይሆናል፦

(1) ኮርሱ በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ሥርዓተ ትምህርት ላይ ስለሌለ/የማይገኝ ከሆነ፣ ተማሪው(ዋ) በሚማርበት/በምትማርበት ትምህርት ቤት የማይሰጥ ከሆነ፣ ወይም ከተማሪው(ዋ) የጊዜ ሰሌዳ ጋር የማይገጣጠም ከሆነ።

(2) ከ MCPS ኮርስ ጋር ተመጣጣኝ የሆነ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ክሬዲት ለማግኘት፣ ተማሪው(ዋ) ኮርሱ መሆኑን ማረጋገጥ አለበ(ባ)ት፣

(a) ለተማሪው(ዋ) ሁሉንም ደረጃ የጠበቀ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ኮርስ/ኮርሶችን ሙሉ እውቀት/ችሎታ ኖሮ(ሯ)ት ለማጠናቀቅ እድል የሚሰጥ መሆኑን ሲረጋገጥ፣

(b) በሞንጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ የሚሰጠውን የጥብቅ ትምህርት መርኅ-የሚመጥን ወይም የሚበልጥ መሆኑ፣ እና

(c) MSDE የተደነገጉ ማናቸውንም ተፈላጊ ሁኔታዎች የሚያሟላ መሆኑ መረጋገጥ አለበት።

(3) ኮርስ ሰጪው ተቋም እውቅና ባለው ኤጀንሲ የፀደቀና MSDE እና MCPS

ዘንድ ተቀባይነት ያለው፣ እናም ኮርሱ MCPS ያፀደቀው መሆን አለበት።

(4) በሜሪላንድ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ላይ ጣምራ ትምህርት የሚማሩ (dually enrolled) ተማሪዎች ካልሆኑ ከዚህ በታች በክፍል III.C.3 እንደተገለፀው ከመደበኛው የትምህርት ቀናት ወይም የትምህርት ዓመት ውጪ ለሚወሰዱ ኮርሶች የወጪዎችን ክፍያ MCPS አይሸፍንም ወይም አስተዋጾ አያደርግም።

3. የጣምራ ትምህርት ምዝገባ/Dual Enrollment

a) የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ተማሪዎች ሆነው እያለ፣ የተወሰኑ መስፈርቶችን እስካሟሉ ድረስ ተማሪዎች በከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ውስጥ ለሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት እና/ወይም ለኮሌጅ ክሬዲት ጣምራ ምዝገባ ሊያደርጉ ይችላሉ። ቢሆንም ተማሪዎች በአንድ ጊዜ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት እና የኮሌጅ ክሬዲት ሊያገኙ የሚችሉባቸው ኮርሶች እና ተማሪዎች የኮሌጅ ክሬዲት ብቻ የሚያገኙትበት አኳኋን እንደሚከተለው ልዩነት አለው፦

(1) ጣምራ ምዝገባ ማለት፡ተማሪዎች የሁለተኛ ደረጃ እና የኮሌጅ ክሬዲት ያገኛሉ ማለት ነው።

(2) አንድ ወጥ የሆነ ምዝገባ ማለት፦ ተማሪዎች በኮሌጅ ትራንስክሪፕት ላይ የኮሌጅ ክሬዲት ብቻ ያገኛሉ ማለት ነው። ለአንድ ወጥ የሆነ ምዝገባ ተማሪዎች ኮርሱን ከመጀመራቸው አስቀድሞ ጣምራ ክሬዲት እንደማይፈልጉ MCPS ቅጽ 280-93፣ ሞልተው ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል።

b) ተማሪዎች ስለ ጣምራ ምዝገባ ወይም አንድ ወጥ የሆነ ምዝገባ እና ስለሚያመለክቱበት ሁኔታ የበለጠ መረጃ ለማግኘት በእያንዳንዱ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የአካደሚክ ካውንስለሮቻቸውን ወይም የጣምራ ኮርስ ምዝገባ ፕሮግራም ድጋፍ ሰጪ እንዲያማክሩ ያስፈልጋል።

c) ለጣምራ ምዝገባ ዓላማየሚከተለው ተፈጻሚ ይደረጋል፦

(1) በሜሪላንድ ህግ እና በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) እንዲሁም በሜሪላንድ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መካከል ባለው የመግባቢያ ስምምነት መሰረት፣ MCPS ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የተመዘገቡ ተማሪዎች MCPS እና በስቴቱ ውስጥ በሚገኝ የህዝብ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በቅድሚያ-የጸደቁ የኮሌጅ ኮርሶችን ያለምንም ወጪ ለመውሰድ መመዝገብ ይችላሉ።

(2) በቅድሚያ የፀደቀ ማለት ከተማሪው(ዋ) የአካባቢ ትምህርት ቤት (ሆም ስኩል) ርእሰ መምህር እና OCIP ተባባሪ ሱፐርኢንተንደንት/ተወካይ የሚከተሉትን በቅድሚያ ማጽደቅ ማለት ነው፦

ጣምራ የተመዘገቡ ተማሪዎች ለ– በቅድሚያ ፈቃድ ማግኘት አለባቸው

(a) ለሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ክሬዲት የኮሌጅ ኮርሶችን ለመውሰድ ወይም በድጋሚ ለመውሰድ፣

(b) የኮሌጅ ኮርስ ለማቋረጥ፣እና

(c) በኮሌጅ ኮርስ ከወደቁ፣ ወይም ኮርሱን ያለቅድሚያ ፍቃድ ካቋረጡ፣ ሌሎች የኮሌጅ ኮርሶችን ያለቅድሚያ ፍቃድ ለሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲት መውሰድ አይችሉም።

(3) በቅድሚያ ተቀባይነት ካገኘ፣ አንድ ተማሪ ለእያንዳንዱ በቅድሚያ-የጸደቀ 3- ወይም 4-ክሬዲት (ወይም ከዚያ በላይ) የኮሌጅ-ደረጃ ኮርስ በተሳካ ሁኔታ ካጠናቀቀ(ች) ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ለመመረቅ ከሚያስፈልገው/ከሚያስፈልጋት 22-ክሬዲት የማሟላት መስፈርት1.0 የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ክሬዲት ያገኛል/ታገኛለች። (ከአራት ክሬዲት በላይ ዋጋ ስለሚኖራቸው የኮሌጅ ኮርሶች ተገቢውን የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ክሬዲት በሚመለከት ርእሰ መምህራን ከተባባሪ OCIP ሱፐርኢንተንዳንት/ተወካይ ጋር በመነጋገር መወሰን ይኖርባቸዋል)።

(4) ከኮሌጅ የቅድሚያ ክሬዲት ይዘው ወደ MCPS የሚዛወሩ ተማሪዎች በነበሩበት ትምህርት ቤት ትራንስክሪፕታቸው ላይ የጣምራ ምዝገባ ክሬዲት ያልተመዘገበላቸው ከሆነ፤ እያንዳንዱ የኮርስ ሥራ እየተገመገመ በርዕሰ መምህር እና OCIP ተባባሪ ሱፐርኢንተንደንት/ተወካይ ውሳኔ ከተሰጠ ብቻ ክሬዲት ማግኘት ይችላሉ።

4. የኮርስ ክሬዲት ዋጋ፣ ጠቅላላ ድምር፣እና ዲፕሎማ የማግኘት ሂደት

a) ከላይ ክፍል III.C.2 እና 3 ላይ እንደተገለጸው፣ከሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ውጪ ካሉት ተቋማት የተገኙ የኮርስ ክሬዲቶች ተማሪው(ዋ) በኮርሱ ከመመዝገቡ(ቧ) አስቀድሞ ክሬዲት የሚሰጥበት/ክሬዲት የማይሰጥበት መሆኑን በመለየት ምርጫ ካላደረገ(ች) በስተቀር በተማሪው(ዋ) አጠቃላይ የውጤት ድምር ላይ ይጨመራል።

b) ኮርሱ በርእሰ መምህር አማካይነት የኦነር ኮርስ ወይም የላቀ ደረጃ ኮርስ ተደርጎ ከተወሰደ እና የኮርሱን መለያ/ኮድ፣የኮርሱ አይነት የሚያስገኘውን ነጥብ የማያካትት ከሆነ፣ የአማካይ ውጤቱ ነጥብ A፣ B፣ C፣ ወይም D ውጤት ላይ አንዳንድ የኮርስ ነጥብ እየተጨመረ የክፍል አማካይ ውጤት ጋር ይሰላል።

c) በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ "MCPS ደንብ IKC-RA" ላይ በተገለጸው መሠረት ለኮርሱ የተሰጠውን ውጤት በማመዛዘን GPA እና WGPA ስሌት ውስጥ ይካተታል።

d) ከሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ውጪ ባሉ ተቋማት ለመመረቂያ ተፈላጊ መስፈርቶችን አሟልተው ከጨረሱ በኋላ የሜሪላንድ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ዲፕሎማ ለማግኘት የሚያስቡ ተማሪዎች የሚከተሉትን ቅድመ ሁኔታዎች ማሟላት ይኖርባቸዋል።

(1) ከሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ውጪ ለመመረቅ የሚያበቁ ኮርሶችን ለማጠናቀቅ ያላቸው እቅድ አስቀድሞ በአካባቢ ት/ቤት ርእሰ መምህር በጽሑፍ መፅደቅ ይኖርበታል።

(2) ኮርሱን የሚሰጠው የትምህርት ተቋም ክሬዲት እና/ወይም ዲፕሎማ ከመሰጠቱ በፊት ተማሪው(ዋ) በኮርሱ ላይ ያገኘ(ች)ውን ውጤት ሪፖርት መስጠት አለበት።

(3) ዲፕሎማዎች የሚሰጡት በአካባቢ ት/ቤት ስም ስለሆነ የዚያ ት/ቤት ርእሰ መምህር ፊርማ ሊኖርበት ይገባል።

D. ከት/ቤት ውጪ ከሙያ ሥራ ጋር የሚገናኙ ልምዶች

1. ከት/ቤት ውጪ በክፍያም የተሠራ ሥራ ልምድ ወይም ያለክፍያ የተሠራ የሥራ-ልምድ ክሬዲት ለማግኘት፣ተማሪው(ዋ) በቅድሚያ አግባብነት ባለው MCPS ኮርስ መመዝገብ አለበ(ባ)ት (ለምሳሌ፦ ኢንተርንሺፕ ወይም MCPS እውቅና የሚሰጠው የሙያ-ሥራ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ኮርስ መጽሔት (Bulletin) ፣ከመስክ ሥራ ጋር የተገናኘ ማስተማር እና ቁጥጥርን ያካትታል።

2. ለእንደዚህ ዓይነት MCPS ቁጥጥር የሚያደርግበት እና ከት/ቤት ውጪ ለሚደረግ የሥራ ወይም የሙሥክ ሥራ ልምምድ፣መመረቂያ መስፈርት ለማሟላት ለአንድ ተማሪ በምርጫ ከሚወሰዱ ክሬዲቶች ከዘጠኝ ተመራጭ ክሬዲት በላይ ላይሰጥ ይችላል።

E. በተናጠል የሚወሰድ ትምህርት

1. በግል-በተናጠል የሚሰጥ ትምህርት ተማሪዎች ከዓላማ፣ ግብ፣ ወይም ከደረጃ የሚያልፍ ስኬታማነት ላይ ለመድረስ ወይም ከዚያም በላይ ለማለፍ የሚያስችላቸውን የትምህርት ልምዶችን እድል ይሰጣል። የተናጠል ትምህርት እድሎችን ለማግኘት የሚያስችሉ መስፈርቶች የሚዘጋጁት በት/ቤት የትምህርት ባለሙያዎች ሲሆን እንደአግባቡ ተማሪዎች እና ወላጆች/ሞግዚቶች ይሳተፉበታል።

   a) እነዚህ ተሞክሮዎች በአካባቢው ት/ቤት መደበኛ የትምህርት ክፍሎች የሌሉ ትምህርቶችን፣ ሪሶርሶችን/ማቴሪያሎችን እና ባለሙያዎችን ያስገኛሉ።

   b) በተናጠል የሚወሰዱ ትምህርቶች እንደ ኮርሱ ሁኔታ ከበርካታ ሳምንታት እስከ ሴሚስተር ወይም ከዚያም በላይ የሚረዝም ጊዜ ሊወስድ ይችላል።

   c) የመመረቂያ መስፈርቶችን ለማሟላት አንድ ተማሪ ከአራት ክሬዲቶች የበለጠ የተናጠል ትምህርት ላይሰጠው/ላይሰጣት ይችላል።

2. ከትምህርት ሙያ ሠራተኞች ጋር በመተባበር፣ ርእሰ መምህሩ/ሯ የሚከተሉትን እንዲሟሉ የማድረግ ኃላፊነት አለበ(ባ)ት።

   a) ለተማሪዎች የተናጠል ትምህርት ፕሮግራም (independent study program) የትምህርት ቤት ተሞክሮ አካል መሆኑን ለሁሉም ተማሪዎች፣ ወላጆች/አሳዳጊዎች፣ እና ለሠራተኞች ማሳወቅ፣

   b) ተማሪዎች የተናጠል ትምህርት ፕሮግራም ላይ በፍላጎት ለመሳተፍ የሚያቀርቧቸውን ማመልከቻዎች የአቀራረብ ቅደምተከተል እና የሠራተኞችንና የባጀት መኖር-ያለመኖር ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ተቀባይነት ሊገኝ ወይም ላይገኝም ይችላል።

   c) ክለሳ ማድረግ፣ ማፅደቅ፣ እና ተናጠል ፕሮጀክቶችን መገምገም

d) የጥናት ፕሮጀክትን በሙሉ ወይም በከፊል ከትምህርት ቤት ግቢ ውጭ ለማከናወን የሚቀርብ ጥያቄ ተቀባይነት ሊያገኝ/ተቀባይነት ላያገኝ የሚችል ቢሆንም (ጥያቄውን ለማቅረብ MCPS ቅጽ 560-31 መሙላት ያስፈልጋል፤ ለወላጅ/ለአሳዳጊ የጉዞ ፈቃድ MCPS መጓጓዣ አያቀርብም።)

e) ከትምህርት ቤት ርቆ በሚከናወን የግል-የተናጠል ጥናት ፕሮግራም ላይ ለመሣተፍ ተማሪው(ዋ) ከወላጅ/ሞግዚት ወይም እድሜው(ዋ) ከሚፈቅድ ተማሪ የጽሑፍ ፈቃድ መቅረብ አለበ(ባ)ት።

3. የተናጠል ትምህርት ፕሮግራም ሲዘጋጅ፣ ት/ቤቱ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የማህበረሰቡን መገልገያዎች/ሪሶርሶችን መጠቀም አለበት።

4. ተማሪዎች በአግባቡ የሙያ ፍቃድ ሠርተፊኬት ካለው/ካላት መምህር ጋር በመተባበር ለራሳቸው የተናጠል ትምህርት ፕሮግራም ተነሳሽነትና እቅድ የማዘጋጀት ሃላፊነት አለባቸው። እና የሙያ ፍቃድ ባለው/ባላት መምህር ክትትል እየተደረገ የሙያ ትምህርት መውሰዳቸውን ማረጋገጫ ለወላጆች/ሞግዚቶች ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል።

5. መምህሩ(ሯ) ተማሪው(ዋ) በኮርሱ ዓላማ፣ግቦች፣ወይም ደረጃውን የጠበቀ እውቀት መጨበጡ(ጧ)ን በመገምገም ተገቢውን የኮርስ ውጤት እና ክሬዲት በመስጠት ወደ ርእሰ መምህር የማሳለፍ ኃላፊነት አለበ(ባ)ት።

6. የተማሪው(ዋ)ን የትምህርት ክትትል ሪኮርድ መያዣ ስልት ተዘጋጅቶ የተናጠል ትምህርት ፕሮግራም ለመከታተል የተመዘገቡበትን ጊዜ በትክክል "በትምህርት ገበታ ላይ መገኘታቸውን" ማረጋገጥ አለበት።

F. አራት-ዓመት የመማር አማራጮች

ሌላ አማራጭ የትምህርት እቅድ ካልተነደፈ ወይም እንዲቀርለ(ላ)ት ካልተፈቀደ በስተቀር ከ 8ኛ ክፍል ትምህርት በኋላ ተማሪዎች የአራት ዓመት ትምህርት በአጥጋቢ ሁኔታ ማጠናቀቅ ይኖርባቸዋል።

1. ከሚከተሉት በአንዱ ምክንያት ማስቀረት/ለሌላ ጊዜ ማስተላለፍ/ መተው ሊፈቀድ ይችላል።

a) ተማሪው(ዋ) የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ከመመረቁ(ቋ) አስቀድሞ እውቅና ባለው ኮሌጅ ተቀብለው(ዋ)ት ከሆነ።

b) ከሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ምረቃ በፊት ተማሪው(ዋ) ለተፈቀደለ(ላ)ት የሙያ/ቮኬሽናል፣ የቴክኒክ፣ ወይም ድህረ-ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ፕሮግራም ለመግባት ተቀባይነት ያገኛል/ታገኛለች።

c) ተማሪው(ዋ) ወደ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የገባ(ች)ው የክፍል ተማሪዎች ካላቸው እድሜ ከፍ ብሎ(ላ) ባለው/ባላት የእድሜ ቅደምተከተል ነው።

d) ተማሪው(ዋ) ሁሉንም የመመረቂያ መስፈርቶች ያጠናቅቃል/ታጠናቅቃለች።

2. ከፈተና በኋላ የሚሰጥ ክሬዲት

በአልጄብራ 2 ወይም እንግሊዝኛ 12 በስተቀር (በሁለቱም ሳይሆን) ሁሉንም ለመመረቅ የሚያስችሉ መስፈርቶችን ያሟሉትን ተማሪዎች ስቴቱ ባፀደቀው ፈተና እና ከ MSDE በተገለፀው

መሠረት ማለፊያ ውጤት አግኝተው ክሬዲት እንዲያገኙ MSDE ይፈቅዳል።

3. ሌላ አማራጭ የምዝገባ ሂደቶችን እቅድ ለማዳበር እና ማስቀረት/ለሌላ ጊዜ ማስተላለፍን የማጽደቅ ሂደት/ፕሮሲጀር እንደሚከተለው ይሆናል።

a) ብቃት ያለው ተማሪ ወይም ወላጅ/ሞግዚት MCPS ቅጽ 280-97 ማግኘትና መሙላት፣ ለአራተኛ ዓመት የመግቢያ ተፈላጊ መስፈርቶችን ለማስቀረትእና ቅጹን ለት/ቤት ካውንስለር ከወቅታዊ MCPS ቅጽ 560-45 ጋር ማቅረብ፣የተማሪ የትምህርትና የእቅድ ሠንጠረዥ በአንድ ፕሮግራም ወይም ኮርስ ለመግባት ከታሰበው ቢያንስ አንድ ሙሉ ሴሚስተር ለውሳኔ አሰጣጥ እንዲያመች በቂ ጊዜ በመስጠት መቅረብ አለበት።

b) ስለታሰበው ፕሮግራም የት/ቤቱ ካውንስለር ከተማሪው(ዋ)፣ እና ወላጅ/ሞግዚት ጋር ለመነጋገር የስብሰባ ጊዜ ቀጠሮ ይይዛል/ትይዛለች። የት/ቤት ካውንስለር አስተያየታቸውን ወደ ርእሰ መምህር ያስተላልፋል/ታስተላልፋለች። ኮሌጅ፣ ቮኬሽናል/የሙያ ትምህርት፣ የቴክኒክ፣ ወይም ድህረ-ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተቀባይነት ወዳለው ተቋም ለመግባት እንዲችል/እንድትችል እንዲፀድቅ አስተያየት ሊወሰን ይችላል።

c) የሱፐር ኢንተንደንት ተወካይ እንደመሆኑ/ኗ መጠን ርእሰመምህሩ/ሯ በማፅደቅ ወይም ባለማፅደቅ MCPS ቅጽ 280-97 ቅጿውን አራተኛ ዓመት ለመቀጠል ተፈላጊው መስፈርት እንዲቀር የቀረበውን ጥያቄ የመጨረሻውን ውሳኔ ለተማሪው(ዋ) እና ለወላጅ/ሞግዚት መግለጽ።

G. የዲፕሎማ ማረጋገጫዎች

የከፍተኛ ችሎታ አገልግሎት ሠርተፊኬት

የከፍተኛ ችሎታ አገልግሎት ሠርተፊኬት ማለት 240 ወይም የበለጠ የተማሪ አገልግሎት ትምህርት (SSL) ሰዓቶችን ላጠናቀቁ ተማሪዎች ከሜሪላንድ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ዲፕሎማ ጋር የሚሰጥ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሠርተፊኬት ነው። በምረቃ ወቅት ለተመራቂዎች የአገልግሎት ልዩ እውቅና የሚያሰጥ አገልግሎት ይለያል።

2. የሞንጎመሪ ካውንቲ የህዝብ ት/ቤቶች የከፍተኛ ችሎታ ሠርተፊኬት

MCPS የከፍተኛ ችሎታ ሠርተፊኬት የሚከተሉትን ተጨማሪ አገልግሎቶች በስኬታማነት/በጥሩ ውጤት ሲያጠናቅቁ ከሜሪላንድ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ዲፕሎማ ማረጋገጫ ጋር የሚሰጥ ሰርተፊኬት ነው።

a) 3.0 አማካይ ከፍተኛ ነጥብ ወይም ከዚያ በላይ ነጥብ ያለው/ያላት፡-

b) MCPS አልጀብራ 2 ኮርስ ክሬዲት ያገኘ(ች)

c) MCPS የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የኮርስ ዝርዝር መጽሔት ላይ ጠንካራ ተብለው የተመደቡ ኮርሶች ላይ ቢያንስ 12 ክሬዲት ያገኘ(ች)

3. የሜሪላንድ የመድብለ ቋንቋ ከፍተኛ ችሎታ

የሜሪላንድ የመድብለ ቋንቋ መለያ ማለት በከፍተኛ ደረጃ መስማት/ማዳመጥ፣ መናገር፣ ማንበብ፣

እና መጻፍ ከእንግሊዝኛ ሌላ/ተጨማሪ አንድ ወይም የበለጠ ቋንቋዎችን ለሚችሉ ተማሪዎች ሽልማት እንዲሰጥ በሜሪላንድ ህግ የተፈቀደ እውቅና መስጠት ነው።

a) የሜሪላንድ ከፍተኛ የመድብለ ቋንቋ ችሎታ እውቅና መስጠት የተመሠረተው በቋንቋ ትምህርት የጠለቀ ችሎታ ምዘና ያለፉትን እውቅና ለመስጠት እና ስለ ከፍተኛ ችሎታቸው ሽልማት ለመስጠት ነው።

b) MSDE የብቃት መስፈርቶችን እና ለእነዚያ መስፈርቶች የብቃት መመዘኛ ፈተና ያዘጋጃል።

c) የዲፕሎማ ማረጋገጫው ለሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ተማሪዎች የሚሰጥ ሲሆን 2017 እና ከዚያ በኋላ ከሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ለሚመረቁ ይሰጣል።

H. የሜሪላንድ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ፕሮግራም ማጠናቀቂያ ሠርተፊኬት

የሜሪላንድ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ፕሮግራም ማጠናቀቂያ ሠርተፊኬት ስንክልና ያላቸው እና የዲፕሎማ መስፈርቶችን ለማሟላት የማይችሉ፣ነገር ግን ከዚህ በታች የተገለጹትን በሜሪላንድ ህግ የተቀመጠ የስቴት ድንጋጌዎችን ለሚያሟሉ ተማሪዎች የሚሰጥ ሠርተፊኬት ነው።

1. የግላዊ ትምህርት ፕሮግራም (IEP) ቡድን ተማሪው(ዋ) በተለዋጭ የትምህርት ውጤቶች እንደሚገመገም "MCPS Curriculum 2.0" ትምህርት መግባት እንዳለበ(ባ)ት፣ ምዘና እንደሚደረግ፣እና የማጠናቀቂያ ሠርተፊኬት እስከሚወስን ድረስ ሁሉም ተማሪዎች እንደ ዲፕሎማ ተማሪ ይቆጠራሉ፣ይገመገማሉ ውጤትም ይሰጣቸዋል። "Annotated Code of Maryland, Education Article, § 8-405(f)" ላይ ከተገለጸው በስተቀር፣ እንዲህ ዓይነቱ ውሳኔ ከወላጅ/ሞግዚት በጽሑፍ የተረጋገጠ ስምምነት ያስፈልገዋል።

2. ተማሪው(ዋ) ከ 8ኛ ክፍል በላይ ቢያንስ ለአራት ዓመት የትምህርት ፕሮግራም እየተከታተለ(ች) ሳለ በግላዊ የትምህርት ፕሮግራም IEP ቡድን በተማሪው(ዋ) ወላጆች/ሞግዚቶች ስምምነት ግለሰቡ(ቧ) ወደ ትክክለኛው የሥራ ዓለም በመግባት፣ ሃላፊነት የሚሰማው(ት) ዜጋ፣እንዲሆን/እንድትሆን፣ ህይወቱ(ቷ)ን በደስታ እንዲ(ድት)መራ የሚያስችለው/የሚያስችላት እውቀት እንዲያጎለብት/እንድታጎለብት የሚጠቅም ሲሆን ነገር ግን በዚህ ብቻ የተገደበ አይደለም—

    a) ጠቃሚ ሥራ፣

    b) ድህረ-ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት እና ስልጠና፣

    c) ድጋፍ የሚሰጥበት የሥራ ቅጥር፣ እና

    d) ሌሎች ከማህበረሰቡ ጋር የተቀናጁ አገልግሎቶች።

3. ተማሪው(ዋ) ከ 8ኛ ክፍል በኋላ ለአራት ዓመት ወይም ከእድሜው(ዋ) ጋር የሚመጥን የትምህርት ፕሮግራም የገባ(ች) ከሆነ እና በዚህ የትምህርት ዓመት ማብቂያ ላይ 21 ዓመት የሚሞላው(ት)።

4. የተማሪው(ዋ)ን የሙያ ትምህርት/እውቀት የሚገልጽ የማሰናበቻ ሠነድ ከሜሪላንድ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ማጠናቀቂያ ሠርተፊኬት ጋር አባሪ መደረግ አለበት።

5. ተማሪው(ዋ) የመጨረሻውን የትምህርት ዓመት በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ከመጀመሩ በፊት ስንክልና ላለበ(ባ)ት ተማሪ የሜሪላንድ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ማጠናቀቂያ ሠርተፊኬት ፕሮግራም ውሳኔ አይሰጥም።

6. ከባድ የመረዳት ስንክልና ያለበ(ባ)ት ተማሪ ለሜሪላንድ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ዲፕሎማ መመረቂያ መስፈርቶችን አያሟላም/አታሟላም ይሆናል፣ተማሪው(ዋ) —

    a) በአማራጭ የአካደሚ ክንውን በአማራጭ የምዘና ደረጃ ከተሳተፈ/ች፣ እና

    b) የአማራጭ ትምህርት ክንውን ደረጃ በመጠበቅ በአማራጭ የአካደሚ ትምህርት በሁለተኛ ደረጃ እስከሚ(ምት)ጨርስ ይቀጥላል/ትቀጥላለች።

***ተዛማጅ ምንጮች፡-*** Annotated Code of Maryland, Education Article §7-103, §7-205, §8-405(f). §18-14A-01, §18-14A-04; Code of Maryland Regulations (COMAR) §13A.03.02 et seq., §13A.07.03.01-.05, and §13B.07.02.01C; Montgomery County Public Schools High School Course Bulletin and associated addenda

***የዚህ ደንብ ታሪክ፡-*** የመጀመሪያው ደንብ ቁጥር 310-3 ማርች 22 ቀን 1976፣ ዲሰምበር 1986 ተሻሽሏል። ሜይ 17 ቀን 1988 ተሻሽሏል። ጁላይ 20 ቀን 1994 ተሻሽሏል። ጁላይ 23 ቀን 1997 ተሻሽሏል። ሜይ 14 ቀን 2008 ዓ.ም ተሻሽሏል፣ ፌብሩዋሪ 14, 2011 ተሻሽሏል፣ ጁላይ 1, 2013 ተሻሽሏል፣ ጁላይ 26, 2017 ተሻሽሏል፣ ኦክቶበር 24, 2017 ተሻሽሏል፣ ማርች 9, 2022ተሻሽሏል፣ ጃኑዋሪ 26, 2024 ተሻሽሏል።

# የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የፀረ-መድሎአዊነት መግለጫ

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) በዘር ሐረግ፣ በጎሣ፣ በቀለም፣ በትውልድ ሐረግ፣ በዜግነት፣ በሃይማኖት፣ በስደት ሁኔታ፣ በጾታ፣ በጾታ መገለጫ፣ በጾታ ማንነት፣በጾታዊ ዝንባሌ፣በቤተሰብ መዋቅር/የወላጅነት ሁኔታ፣ በትዳር ሁኔታ ላይ የተመሰረተ ሕገወጥ አድልዎ ማድረግን ይከለክላል። ዕድሜ፣ ችሎታ (ግንዛቤ፣ ማህበራዊ/ስሜታዊ እና አካላዊ)፣ ድህነት እና ማህበራዊ-ኢኮኖሚያዊ ደረጃ፣ ቋንቋ፣ ወይም ሌላ በህግ ወይም ህገ-መንግሥታዊ ጥበቃ የተደረገላቸው ባህሪያት ላይ የሚደረግ ማናቸውንም ሕገወጥ አድልዎ ይከለክላል። መድሎ ወይም አድሎአዊነት፤ ሕብረተሰባችን ለረዥም ጊዜ እኩልነት፣ ፍትኃዊነት፣ አብሮነት፣ ሁሉን አቀፍነትን፣ ለማስፈን እና ለማዳበር/ለመንከባከብ ሲካሄድ የቆየውን ጥረት ይሸረሽራል/ያበላሻል። ቦርዱ ጥላቻን የሚያራምድ ቋንቋን እና/ወይም ምስሎችን እንዲሁም ምልክቶችን መጠቀምን ይከለክላል፥ በተለይም በትምህርት ቤት ወይም በዲስትሪክት ሥራ ወይም እንቅስቃሴ ላይ ከፍተኛ ማደናቀፍ ሊያስከትል የሚችል ድርጊት-እንቅስቃሴ የተከለከለ ነው። የበለጠ መረጃ ለማግኘት፣ እባክዎ የሞንትጎመሪ ካውንቲ "የትምህርት ቦርድ ፖሊሲ ACA" ይመልከቱ፡- "ከአድሎአዊነት ነጻ የሆነ ፍትሃዊነት፥ ሚዛናዊነት፥ እና የዳበረ ባህል"። ይህ መመርያ እያንዳንዱ ተማሪ ትኩረት የሚሻ መሆኑ(ኗ)ን እና በተለይም የትምህርት ውጤቶች በምንም አይነት በግለሰብ ትክክለኛ ወይም ይሆናል ተብሎ በሚገመት ግላዊ ባህርያት የሚተነበይ እንደማይሆን የቦርዱን እምነት ያረጋግጣል። ፖሊሲው በተጨማሪም ፍትህ/እኩልነትን/ሚዛናዊነትን የሚያዛቡ ነገሮችን ለይቶ በማወቅ በቅድሚያ መወሰድ ያለባቸው እርምጃዎችን፥ የተዛባ ስውር አመለካከትን፣ ጭፍን/መሠረተ-ቢስ ልዩነት ማድረግን፣ በተቋማት የሚፈጸሙ መዋቅራዊ መሰናክሎችን፣ በትምህርት እና በሥራ ላይ እኩልነት እንዳይኖር ተፅእኖ የሚያደርጉ አሠራሮችን የሚገታ/የሚፃረር መሆኑን ያስገነዝባል። MCPS ለወንድ/ለሴት ልጆች በስካውትነት እና በሌሎች የወጣት ቡድኖች ለመመደብ እኩል ተደራሽነት ይሰጣል።

A. በሜሪላንድ ስቴት ፖሊሲ መሠረት ሁሉም የህዝብ እና በህዝብ የገንዘብ ድጋፍ የሚደረግላቸው ትምህርት ቤቶች እና የትምህርት ቤት ፕሮግራሞች የሚከተሉትን ድንጋጌዎች በማክበር መንቀሳቀስ አለባቸው፡-
   (1) 1964 የፌደራል ሲቪል መብቶች ህግ አንቀጽ VI፣ እና
   (2) በሜሪላንድ ኮድ የትምህርት ደንብ አንቀጽ 26 ንዑስ አንቀጽ 7፣ ይኼውም የህዝብ እና በህዝብ የገንዘብ ድጋፍ የሚደረግላቸው ትምህርት ቤቶች እና ፕሮግራሞች፡-
      (a) በዘር፣ በጎሳ፣ በቀለም፣ በሃይማኖት፣ በጾታ፣ በእድሜ፣ በብሔር፣ በጋብቻ ሁኔታ፣ በፆታዊ ሁኔታ፣ ዝንባሌ፣ የፆታ ማንነት፣ ወይም የአካል ጉዳተኝነት ምክንያት፣ አሁን ባሉት ተማሪዎች ላይ፣ የወደፊት ተማሪዎች ላይ፣ ወይም የአሁን ወይም የወደፊት ተማሪዎች ወላጆች ወይም አሳዳጊዎች ላይ አድልዎ ማድረግ የተከለከለ ነው፣
      (b) በአንድ ግለሰብ ዘር፣ ጎሳ፣ ቀለም፣ ምክንያት የወደፊት ተማሪዎችን መመዝገብ እምቢ ማለት፣ የአሁኑን ተማሪዎች ማባረር፣ ወይም ከአሁን ተማሪዎች፣ የወደፊት ተማሪዎች ወይም የአሁኑ ወይም የወደፊት ተማሪዎች ወላጆችን ወይም አሳዳጊዎችን የሃይማኖት፣ የጾታ፣ የዕድሜ፣ የብሔር፣ የጋብቻ ሁኔታ፣ የፆታ ዝንባሌ፣ የፆታ ማንነት ወይም የአካል ጉዳት፣ የመሳሰሉትን ምክንያት በማድረግ መብቶችን መከልከል፣ ወይም
      (c) የትምህርት ውጤቱ(ቷ) ምንም ይሁን ምን መርሃ ግብሩ ወይም ትምህርት ቤቱ በተማሪው(ዋ) ላይ አድሎአዊነትን ፈጽመዋል የሚል ቅሬታ ባቀረበ(ች) ተማሪ ወይም ወላጅ ወይም አሳዳጊ ላይ ቅጣት ማድረግ፣ ወይም ማንኛውንም ሌላ የበቀል እርምጃ መውሰድ የተከለከለ ነው**

እባክዎን የግንኙነት መረጃ እና የፌዴራል፣ የስቴት፣ ወይም የአካባቢ መረጃ ይዘትን በተመለከተ መስፈርቶቹ በዚህ ሰነድ እትም ላይ ተለውጠው ሊሆን ይችላል፥እና በወቅታዊ መረጃ እንደተተካ ልብ ይበሉ። በዚህ ውስጥ የተካተቱትን መግለጫዎች እና ማመሳከሪያዎችን ወቅታዊ መረጃ ለማግኘት እባክዎን ይህንን በይነመረብ ይመልከቱ፡- www.montgomeryschoolsmd.org/info/nondiscrimination

| በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ተማሪዎች ላይ አድልዎ ሲፈጸም ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ አድራሻው ከዚህ በታች የሚገኘው ነው፡-*** | በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሰራተኞች ላይ ስለሚደርስ መድልዎ ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ አድራሻው ከዚህ በታች የሚገኘው ነው፡-*** |
|---|---|
| Director of Student Welfare and Compliance<br>Office of District Operations<br>Student Welfare and Compliance<br>15 West Gude Drive, Suite 200, Rockville, MD 20850<br>240-740-3215 \| SWC@mcpsmd.org | Human Resource Compliance Officer<br>Office of Human Resources and Development<br>Department of Compliance and Investigations<br>45 West Gude Drive, Suite 2500, Rockville, MD 20850<br>240-740-2888 \| DCI@mcpsmd.org |
| 1973 የተሃድሶ ድንጋጌ ሰክሽን 504 መሠረት ለተማሪ የመገልገያ/አኮሞዴሽን/ ጥያቄ ማቅረቢያ አድራሻ ከዚህ በታች የሚገኘው ነው፡- | በአካል ጉዳተኛ አሜሪካውያን ህግ መሠረት ለሰራተኞች የመገልገያ/የአኮሞዴሽን/ ጥያቄ ማቅረቢያ አድራሻ ከዚህ በታች የሚገኘው ነው፡- |
| Section 504 Coordinator<br>Office of School Support and Improvement<br>Well-Being and Student Services<br>850 Hungerford Drive, Room 257, Rockville, MD 20850<br>240-740-3109 \| 504@mcpsmd.org | ADA Compliance Coordinator<br>Office of Human Resources and Development<br>Department of Compliance and Investigations<br>45 West Gude Drive, Suite 2500, Rockville, MD 20850<br>240-740-2888 \| DCI@mcpsmd.org |
| ታይትል IX ስር ስለ ፆታዊ መድልዎ፣ ጾታዊ ትንኮሳን ጨምሮ፣ በተማሪዎች ላይ ወይም በሰራተኞች ላይ ስለሚደረግ ጥቃት ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ አድራሻው ከዚህ በታች የሚገኘው ነው፡-*** | |
| Title IX Coordinator<br>Office of District Operations<br>Student Welfare and Compliance<br>15 West Gude Drive, Suite 200, Rockville, MD 20850<br>240-740-3215 \| TitleIX@mcpsmd.org | |

*ይህ መግለጫ ከተሻሻለው የፌዴራል የአንደኛ ደረጃ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ህግ ጋር የተጣለጠ ነው።
**ይህ መግለጫ የሜሪላንድ ዝርዝር ደንብ/ኮድ አንቀጽ 13A.01.07. ጋር የተጣለጠ ነው።
***የመድሎአዊነት ቅሬታዎችን ለሚከተሉት ሌሎች ኤጀንሲዎችም ማቅረብ ይቻላል፡-

U.S. Equal Employment Opportunity Commission (EEOC), Baltimore Field Office, GH Fallon Federal Building, 31 Hopkins Plaza, Suite 1432, Baltimore, MD 21201, 1-800-669-4000, 1-800-669-6820 (TTY); Maryland Commission on Civil Rights (MCCR), William Donald Schaefer Tower, 6 Saint Paul Street, Suite 900, Baltimore, MD 21202, 410-767-8600, 1-800-637-6247, mccr@maryland.gov; Agency Equity Officer, Office of Equity Assurance and Compliance, Office of the Deputy State Superintendent of Operations, Maryland State Department of Education, 200 West Baltimore Street, Baltimore, MD 21201-2595, oeac.msde@maryland.gov; or U.S. Department of Education, Office for Civil Rights (OCR), The Wanamaker Building, 100 Penn Square East, Suite 515, Philadelphia, PA 19107, 1-800-421-3481, 1-800-877-8339 (TDD), OCR@ed.gov, ወይም www2.ed.gov/about/offices/list/ocr/complaintintro.html.

ይህንን ሠነድ ከእንግሊዝኛ ቋንቋ በተጨማሪ በአማራጭ ቋንቋ/ፎርማት ማግኘት ካስፈለገ "Americans with Disabilities Act" ድንጋጌ መሠረት MCPS Office of Communications በስልክ ቁጥር፡- 240-740-2837፣ 1-800-735-2258 (Maryland Relay) ወይም PIO@mcpsmd.org በመጠየቅ ማግኘት ይቻላል። የምልክት ቋንቋ ትርጉም የሚያስፈልጋቸው ግለሰቦች የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ የትርጉም አገልግሎት ጽ/ቤትን በዚህ ኤሜይል ወይም በስልክ መጠየቅ ይችላሉ። MCPS Office of Interpreting Services ስልክ ቁጥር 240-740-1800, 301-637-2958 (VP) mcpsinterpretingservices@mcpsmd.org, ዐወይም MCPSInterpretingServices@mcpsmd.org

ሀምሌ 2024